# የዴሞክራሲ ባህልና ጉዞ በኢትዮጵያ

ሓጎስ ኣረጋይ(PhD) ሰኔ 21/2009

ከህዝብ የኣስተዳደር ስርዓትና ወግ ተያያዥነት ያለው መስተጋብር ውስጥ ሁለት ፅንፍ የሆኑ ኣስተሳሰቦች ማንሳት ይቻላል ። እነሱም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እና ፍፁም ዴሞክርስያዊ ስርዓት ናቸው። እነዚህን ሁለት ፅንሰ ሃሳቦች እንደመነሻ በመጠቀም የህዝብን የኣስተዳደር መስተጋብራዊ ስርዓት ወዴት እንደሚያመዝን መተቸት የተለመደ ባህርይ ነው። በእርግጥ ዴሞክራሲ በመፈለጉ ብቻ በኣንድ ጀምበር የሚሰጥ ወይም የሚነፈግ እውነታ ኣይደለም ብንል ማጋነን ኣይሆንም ።

ከምእራባውያን እንደምንረዳው ፣ ዴሞክራሲ የማህበረሰባቸው ዕድገት፣ ባህል፣ ንቃተ ህሊና፣ ትምህርት ወዘተ ተዛምዶ እያደገና እየተጠናከረ የመጣ የረዥም ግዜ ሂደት መሆኑን ብዙ ሃተታ የሚያስፈልገው ኣይመስለኝም። የኣገራችንስ ሁኔታ እንዴት እንረደዋለን? በእርግጥ የዚች ፅሁፍ ማጠንጠኛ የዲሞክራሲ ባህልና ጉዞ በኢትዮጵያ ቢሆንም የማህበረሰቡ ኢኮኖሚ፣ ትምህርት ወዘተ ለዴሞክራሲ እድገት ወሳኝ ሚና እንዳለው ከምእራባውያን ዴሞክራሲ መገንዘብ ችለናል ። በመሆኑም በኣገራችንም በየወቅቱ የነበረውን የማህበረሰባችን የኢኮኖሚ መዋቅርም በተወሰነ መልኩ ይንፀባረቃል ማለት ነው።

ስለዚህ ታሪካችን የኣክሱምን ዘመነ መንግስትም ጭምር ስለ ሚያካትት ኣጠር ባለ መልኩ ማንሳቱ ተገቢ ነው እላለሁ። በኣክሱም ዘመነ መንግስት በስልጣኔ ማማ ላይ የደረሰ ማህበረ ሰብ እንደነበርን ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ነው። የነበረው የስልጣኔው ምጥቀት ከሚያሳዩት መካከል፥

- ዕፁብና ድንቅ ጥበብ ያረፈባቸው ሓወልቶች
- የተለያዩ ዓይነት፣ ቅርፅና ይዘት ያለው መገበያያ ገንዘብ

እንደማሳያ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ የስልጣኔ ኣሸራዎቻችን ተንከባክበን ያቆየናቸው ሳይሆን የተፈጥሮ (ፀሃይ ፣ዝናብ ወዘተ) እና ሰው ሰራሽ (የዮዲት ጉዲት ማፍረስ ተግባር ወዘተ) ተቋቁመው ኣሁንም ቢሆን የኣሰራራቸው ምጥቀትና ውበት ኣሁንም ምስጢር እንደሆነ ነው። በመጨረሻም፣ ለኣክሱም መንግስት ውደቅት ሰበብ የሆነቸው ዮዲት ጉዲት እንደሆነች ይነገራል።

የኣክሱም መንግስትን መውደቅ ተከትሎ የዛግዌ ስርወ መንግስት ተተካ። የዛግዌ ስርወ መንግስት የክሱምን የስልጣኔ ኣሸራ ተከትሎ የላሊበላ ውብና ዕፁብ የሆኑ ውቅር ኣብያተ ክርስቲያናት ለመስራት በቅተዋል። ልክ እንደ ቁሳዊ ኣሻራችን ሁሉ፣ የገዳ የህዝብ የኣስተዳደር ስርዓትም የሰው ሰራሽ ችግሮችን ተቋቁሞ የሚታይና የሚደመጥ እውነታ ነው ብንል ማጋነን ኣይሆንም። ስለዚህ የገዳ ስርዓት ኣሁንም በኦሮምያ እየጠቀሙበት እንደሆነ በቴሌቭዥን እያዩን ነው። በመሆኑም ብዙውን ግዜ ወደ ምእራቡ ኣለም ከምናተኩር ይልቅ በገዳ ስርዓት የሚንፀባረቁ ፅንሰ ሃሳቦች በጥናትና ምርምር ተለይተው ለዲሞክራስያዊ ስርዓታችን ግንባታ የራሱ የሆነ ኣስተዋፅኦ ይኖረዋል ብዬ ኣስባለሁ ።

የዛግዌ ስርወ መንግስትን የመተካት ሂደትና ከዚያ በኋላ የነበረው የአስተዳደር ስርዓት አጠር ባለመልኩ ማየት ብንችል የዴሞክራሲያችን ባህልና ጉዞ ከሞላ ጎደል ያሳየናል ብዬ አስባሎሁ፡፡ በመሆኑም ለፅሁፌ መንደርደሪያ ይሆነኝ ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንስቻሎሁ ፡፡

- ከአገራችን ታሪክ አንፃር ሲታይ ዴሞክራሲ እንዴት ነው የምንገነዘበው ?
- ለዴሞክራሲ መጎልበት መወሰድ ያለበት እርምጃ ምንድነው ነው? ለምን?
- ዴሞክራሲ በማህበረሰብ ልማትና ተግባቦትን ያለው እንድምታስ ምንድነው?

በሚሉ ጥያቄዎቸ በመንተራስ የተለያዩ ማስረጃዎችን በማጣቃስ ለመግለፅ ወደድኩኝ፡፡ በመሆኑም እንደየ ስርዓቱ ባህርይ በሶስት ዋና ዋና ርእሶች ለማቅረብ ወሰንኩኝ፡፡ እነሱም የአፄዎች (የሰሎሞናዊ ዘውግ መንግስት) ፣ የደርግና የኢህዴግ ስርዓቶች ናቸው ፡፡

## 1. በአፄዎች የዴሞክራሲ ባህልና ጉዞ

ከ 1270 (አካባቢ)–1966 ዓ/ም (ለ 700 ዓመታት ያክል)፣ ሰዎች ናቸው የተቀያዬሩት እንጂ የነበረው ስርዓት በብዙ መልኩ አንድ ዓይነት ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ በመሆኑም ከዛግዌ ወደ ሰሎሞናዊ ዘውገ መንግስት የተሻገረበት አግባብ፣ በዝዔዎቹ የነበረው የመስተዳድር ሞዴል (ስርዓት) ገላጭ በመሆኑ አጠር ባለመልኩም ቢሆን መግለፁ ተገቢ ነው እላሎሁ፡፡ ስለዚህ ፣

**ከዛግዌ ወደ ሰሎሞናዊ ዘውገ መንግስት ለመሻገር ይንፀባረቅ የነበረው ማጠንጠኛው ሃሳብ የሚያሳየው ፣ ንግስነት/ መንግስትነት ለሰሎሞናዊ ዘውግ እንጂ ለኩሻውያን (አገዋውያን) አይገባም የሚል ነበር ፡፡ ይህንን መሰረተ ሃሳብ በመያዝ በወቅቱ ከነበሩ የሃይማኖት አባቶች በሃሳብ ተጋብተው በዛግዌ ስርወ መንግስት ዘሙቱ (አመፅ አስነሱ)፡፡ በአመፁ ምክንያት የዛግዌን ስርወ መንግስት ንደው የሰሎሞናዊ ዘውገ መንግስት አቋቋሙ፡፡ በሰሎሞናዊ ዘውገ መንግስትነት ስም አፄ ዩኩኖ አምላክ የተባሉ ሰው በ 1270 አካባቢ የመንግስትን በትረ ስልጣን ለመጨበጥ በቁ ( ዶ/ር ሃበተማርያም(1986) ገፅ 282 ላይ ጀምሮ በዝርዝር ሰፍረዋል) ፡፡**

የህዝብ የአስተዳደር ስራ (ንግስነት) በፈጣሪ አምላክ ለሰሎሞናዊ ዘውግ ብቻ የተሰጠ ፀጋ ነው በሚል ሃሳብ በወቅቱ ከነበሩ የሃይማኖት አባቶች ቁርኝት ፈጥረው አራገቡት፡፡ ቀጥሎም ወደ መንበረ ስልጣንም ተቆናጠጡ፡፡ ስለ ንጉሳውያን በነበረው የስብከት ሂደትም ነጥረው የወጡ ገዢ ሃረጋት መካከል፣

- ተሰርዓ በሰማያት ተሰርዓ በምድር
- ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ
- ንጉስ ስዩመ እግዚአብሄር ነው
- ንግስነት የእግዚአብሄር ፀጋ ነው

የሚል ኣስተሳሰብ በህበረተ ሰቡ እንዲሰርፅ ተደረገ ። ነገሩ ከእምነት የተያዬዘ በመሆኑ ህብረተ ሰባችን ቢወድም ባይወድም መቀብል ግድ ሁኖበት ነበር ማለት ይቻላል ። በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ ለ700 ዓመታት ያህል <u>**በመለኮታዊ የእዝ ሰንሰለት የስልጣን ተዋረድ**</u> ቀንበር ስር ወደቀን ። በመለኮታዊ የእዝ ሰንሰለት ስልጣን ያልኩበት ዋና ምክንያት ከግል ኣመለካከቴ ሳይሆን እንደ ኣውሮፓ ኣቆጣጠር በ 1955 ዓ/ም ተሻሽሎ የወጣው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት የሚለውን እጠቅሳሎሀ " **Conquering lion of the Tribe of Judah Haileselasie I elect of God, Emperor of Ethiopia"** የትርጉሙ ይዘት ባጭሩ ከሰሎሞናዊ ዘውግ በመሆኔ በፈጣሪ ኣምላክ የተመረጥኩ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነግስት ነኝ የሚለውን መልእክት ያስተጋባል ። ከዚህ በተጨማሪ ለኣፄ ሃ/ስላሴ ሰዎች እንደ ፈጣሪ ይሰግዱላቸው እንደነበር የሚያሳይ ሁሌም በኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሪሽን (ተለቪዥን) መስኮት ይታያል። ካላዩም በተለያዩ ወቅት ስለሚተላለፍ መመልከት ይቻላል።

በመለኮታዊ እዝ ባለስልጣናት የሆኑና ኣሽከሮቻቸው ሰርተው ከሙብላት ይልቅ ከኣንዱ ወደ ኣንዱ እየተዘዋወሩ የገበሬው ሃብት ሙብላት፣ ልክ የሌለው ግብር የማስከፈልን ስራ ተያያዙት ( ዶ/ር ሃብተማርያም (1986) እንዳስቀመጡት)። በኣጠቃላይ የእደ ጥበብ ስራዎች ከማበራታት ይልቅ የማንኳሰስ ስራ ቀዳሚ ኣጀንዳቸው እንደነበር መርጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ ቡዳ፣ ቆዳ ፋቂ ፣ ኣንጠረኛ ፣ ሸማኔ፣ ወዘተ የሚል ታርጋ በመለጠፍ ለእደ ጥበብ ስራዎች ዘርፍ መዳካም ከፍተኛ ሚና ነበራቸው ብንል ማጋነን ኣይሆንም።

ኣልፎ ኣልፎ የስልጣኔ ጮራ ብቅ ካለም በጉልበት እንዲጠፋ ያደርጉ ነበር። ለምሳሌ ዘፀኣት "በደቂቀ እስጢፋኖስ ሊገለጥ የነበረው የኢትዮጵያ ኣብርሆት (Enlightenment)- እጅግ የሚያስቆጭ ያመለጠን ኣጋጣሚና.. " በሚል ርእስ በኣይጋ ፎሮም የወጣው ፅሁፍ በግልፅ ያሳያል። ፅሁፉ እንደሚያስረዳው ማእከላቸው ትግራይ ሁኖ በሳይንስና በዴሞክራሲ ኣንድ እርምጃ ወደፊት የተራመዱ በደቂቀ ኢስጢፋኖስ የሚጠራ ኣዲስ ኣስተሳሰብ እንደነበር ያትታል። እነዚህ ሰዎች በሳይንስና ዴሞክራሲ ካነሱዋቸው መካከል፣

- በዴሞክራሲ ዘርፍ፣
  - ✓ ለፈጣሪ ካልሆነ በስተቀር ለማንም መስገድ የለብንም
  - ✓ ሃይማኖትና መንግስት መለያየት ኣለባቸው
  - ✓ ሲሶ ለነጋሽ፣ ሲሶ ለአራሽ፣ ሲሶ ለቀዳሽ" የሚለውን ኣዋጅ በፅኑ ተቃወሙ
- በሳይንስ ዘርፍ ከተጠቀሱት መካከል
  - ✓ በኣለም ለመጀመርያ ግዜ ሊባል በሚችል መልኩ ብርትኳንና ሌላ እስከኣሁን ያልታወቀ ተክል በማዳቀል የጉንዳጉንዶ ጣፋጭ ብርቱካን የሚባለውን ኣምርተዋል፣
  - ✓ በዐለም የመጀመርያው የሆነው ሊባል በሚችል መልኩ በነፋስ ሐይል የሚሰራ የውሓ መዘውር ሰርተዋል፤
  - ✓ አስገራሚ የእርሻ ጥበቦች (መስኖ እርሻ)፣ ትልልቅ የውሃ ማስተላለፍያ ድልድዮችና ትቦዎች መዘርጋት ችለዋል፤

የደቂቀ እስጢፋኖስ ስራዎችና ኣስተሳሰቦች በትግራይ ህዝብ ብዙ ተከታይ ኣግኝተው እንደነበረ ፅሁፉ የሚያትተው። ነገር ግን ዓፄ ዘርዓ ያእቆብ ((1426-1460) ይህንን ጉልህና ግልፅ የሆነ የስልጣኔ ጮራና ኣስተሳሰብ በጉልበት እንዲከስም ኣደረጉ። የፈነጠቀው የስልጣኔ ጮራ ብቻ ሳይሆን የኣስተሳሰቡ ተከታይ የነበረው የትግራይ ህዝብም እንዲጨፈጨፍ ኣደረጉ።

**ከስልጣኔ ጮራ ማከሰም ባሻገር አፄዎቹ** በሰዎች ማንነትና ባህል ዘመቻ ከፍተው አበሳብሰዋል። በመሆኑም ከአማራ ብሄር ውጭ የሆነውን ቋንቋ፣ ባህል፣ ወዘተ የኋላቀር ምልክት አድርገው ይወስዱት ነበር። ከዚህ በመነሳት **ዋለልኝ መኮነን** በማያሻማ ቋንቋ የነበረውን ሁኔታ ገልፆታል። ዋለልኝ እንዳለው ኢትዮጵያዊ ለመሆን የገገር መዶቦችን አስተሳብ መከተል ግድ እንደነበር ። እንዲሁም ኢትዮጵያ የብሄር በሄረ ሰቦች እስር ቤት እንደሆነች በአጭርና ግልፅ የሆነ ፅሁፍ አስቀምጠዋል ። በዚህ ጉዳይ ላይ "ኢትዮጵያና የዘረኝነት ልክፍት" በሚል ርእስ በ 09/06/2017 ከ ገፅ 4-8 ማስረጃውን በማጣቀስ በአይጋ ፎረም ፖስት ተደርገዋልና ማንበብ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ "አንድ አገር አንድ ህዝብ" ይሉ ነበር።ይህንን የሚያመለክተው፣ የመለኮታዊ እዥ ሹማምንቶች የኢትዮጵያን መሬት ብቻ ሳይሆን ህዝቡንም የግል ንብረታቸው እንደሆነ በማሰብ የተራመዱበት ኣግባብ ነበር ማለት ይቻላል። ለማሳያነት ያክል፣ ባርያ(ሎሌ) ብለው የሚጠሩት

- ሰው እንደዕቃ በስጦታ ለሙንሽራ ይሰጥ እንደነበር የኣደባባይ ምስጢር ነው፣
- በገንዘብ ከኣንዱ ወደ ሌላ ጌታ ባርያ ብለው የሚጠሩት ሰው ይሸጥ እንደነበር ይታወቃል።

ኣፄዎቹ " ኣንድ ሃይማኖትም " ይሉ ነበር። ከዚህ የምንረዳው ኣፄዎች እነሱ ከሚከተሉት ሃይማኖት ውጭ የሆነ ሁሉ ቦታ እንደሌለው ያሳያል ።

**በኣጠቃላይ የነበረውን ሂደት ለማነፃፀር ያክል በወቅቱ ፥**

- ራስ የማስተዳደር መብት አልነበረም። በወቅቱ የኣስተዳደር ክልል/ጠቅላይ ግዛት ብለው በሰየሙዋቸው ቦታዎች ሁሉ የሚምስላቸውን ሰው እንደ ራሴ ብለው ይሾሙ ንነበር። እንደ ራሴዎቹ ከኣፄዎቹ የተነገረውን ቃል ኣክብረውና አስከብረው ያስተዳድሩ ነበር። ስለዚህ እንደራሴዎቹ የኣገዛዙ ስርዓት ባለሙዋል ሁኖ ያገለግላሉ ወይም ቢጋብቻ የተሳሰሩ በመሆናቸው እዛው በዛው ነው ስርዓቱ የሚያስኬዱት፣
- ኣልፎ ኣልፎ የመማር እድል ከተገኘም፣ በራስ ቋንቋ የመማር ስርዓት ኣልነበረም። ህፃናት ልጆች በኣፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት ተነፍጎዋቸው በኣማርኛ እንዲማሩ ይደረግ ነበር። ይህ የተደረገበት ምክንያት ኣማርኛ ለሳይንስ ቅርብ በመሆኑ ኣልነበረም ። ይልቁኑስ ኣማርኛ የሰሎሞናዊ ዘውግ መንግስት ቋንቋ በመሆኑና የበላይነታቸው ለማረጋገጥ ነው። ከዚያ በመቀጠል ቀስ ቀስ በቀስ ደግሞ የብሄር ብሄረ ሰቦችን ማንነት ለማጥፋት ታስቦ ነው።
- በራስ ቋንቋ መዳኘት ኣልነበረም። በወቅቱ ብሄር ብሄረ ሰቦች በማያውቁት ቋንቋ ይዳኙ ነበር። ምናልባት ከቻሉ በራሳቸው ወጪ ኣስተርጓሚ ይዘው ይቀርባሉ። ከዚህ በተጨማሪ ኣማርኛ የማይችል ሰው ፋራ የሚል ስያሜ ይሰጠው ነበር።
- ህዝብ እንደህዝብ መንግስትን የመምረጥ መብት ኣልነበረውም። በወቅቱ የነበሩ መንግስታት ስልጣናቸው ከፈጣሪ እንደተሰጣቸው ኣድርገው ህዝቡን ያታልሉ ነበር።
- የፆታ እኩልነት፣ የሃይማኖት እኩልነት ወዘተ ኣልነበረም ማለት ይቻላል

**በመለኮታዊ የእዝ ሰንሰለት በሆነ ስልጣናቸውን በመጠቀም፣**

- ኢትዮጵያውያን ለ 700 ዓመታት ያህል በሃይማኖት ስም የሂሊና እስረኞች ሆኖ እንዲቆዩ ተደርገዋል
- በዛጉዌና ከዚያ በፊት የነበረው የስልጣኔ ጭላንጭልና የዴሞክራሲ ነፀብራቆች እንዲደበዝዙ ወይም እንዲጠፉ ተደርገዋል
- ኣልፎ ኣልፎ ብቅ የሚሉትንና ለስልጣኔ በር ከፋች የሆኑ ኣስተሳሰቦችና የስራ ዘርፎች ተከታትለው የማፅዳት/የማጥፋት ስራ ይሰሩ ነበር ብንል ማጋነን ኣይሆንም ( እንደ እደ ጥበብ፣ በደቂቀ እስጢፋኖስን ወዘተ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል)

በኢኢኮኖሚ ዘርፍ የነበራቸው መሬ እቅድ **ሲሶ ለነጋሽ፣ ሲሶ ለኣራሽ፣ ሲሶ ለቀዳሽ የሚል እንደነበር ይታወሳል።** በመሆኑም ኣፄዎቹ (መኳንንቶቹ) እጃቸውና እግራቸው ኣፅድተው/ሞሽረው ገብሬ ያመረተውን ሃብት ብቻ ቁጭ ብለው መብላትን ነው ስራቸው የነበረ ብንል ማጋነን ኣይሆንም ። ስለዚህ ስለ ኢኮኖሚና ዴሞክራሲያዊ መዋቅራዊ ሽግግር ማሰብ ይቅርና ከለጋሽ ኣገሮች እርዳታ በመለመን ይሁን ከራሳቸው በጀት የ66ቱ የወሎን ድርቅ ለመታደግ ኣልቻሉም ነበር። ይልቁንስ ህዝቡ እያለቀ መሆኑን እንዳይታውቅባቸው ደብቀው በመያዛቸው ምክንያት ህዝቡ በረሃብ እያለቀ እንደነበር ዋይ ዋይ ሲሉ የሚለውን የዶ/ር ጥላሁን ገሰሰ ዘፈን መመልከት በቂ ነው

**እውነት እናውራ ከተባለ ፣**

- **ኣፄ ዩኩኖ ኣምላክ እውን የሰልሎሞን ዘረ ግንድ ኣላቸውን? ለመሆኑ ዘረግንዳቸው ያንን ያህል ርቀት ቀጥረው ያውቁታልን?**
- **ቀዳማዊ ሃይለስላሴ የሰልሎሞን ዘረ ግንድ ኣላቸውን? ለመሆኑ ዘረግንዳቸው ያንን ያህል ርቀት ቀጥረው ያውቁታልን?**

ድፍረት ኣይሁንብኝ እንጂ ኣፄዎቹ ያነሱት ሃሳብ ከማጭበርበር ውጭ ሌላ ትርጉም ያለው ኣይመስለኝም ። ምክንያቱም እግዚኣብሄር ለፈጠረው ሰው ሁሉ ቸር ነው እላለሁ። በመሆኑም እንደኣፄዎቹ ኣባባል፣ ፈጣሪያችን የኣንዱ የዘር ሃረግ በሌላው የዘር ሃረግ ጫንቃ ወጥቶ እንዲጨፍር ይፈቅዳል በዬ ኣላስብም። ፈጣሪ በፍፁም ኣያዳላም ብዬ ኣምናለሁ ። እንኳን ፈጣሪን ያክል ይቅርና ጤናማ ኣስተሳሰብ ያለው ሰውም ቢሆን እንደ ኣፄዎቹ ህዝብን በሃይማኖት ሰበብ ኣጭበርብሮ የዚህ ዘር ኣገልጋይ የዛኛው ዘር ተገልጋይ ብሎ ለ 700 ዓመታት ኣከባቢ ያሰቃያል ፣ ኣገርንም እንደ ኣገር የኋላ ጉዞ እንድትሄድ ያደርጋል ብዬ ኣላስብም ።

ኣንድ ወቅት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በዩ-ቱዩብ የተለቀቀው ንግግራቸው ላይ ቀዳማዊ ሃ/ስላሴና በላይ ዘለቀ ኦሮሞ ናቸው ሲሉ ኣዳመጥኩኝ ። የበላይ ዘለቀ ጉዳይ ለግዜው እንተወውና እና ወደ ቀዳማዊ ሃ/ስላሴ እንመለስ ። ቀዳማዊ ሃ/ስላሴ በህገ መንግስታቸው ላይ የሰሎሞን ዘር ነኝ ብለው ኣስፍረዋል። ኣሁን ደርሶ ኦሮሞ ናቸው ለማለት ለምን ተፈለገ?

እንደ እኔ ኣመለካከት ዘራቸው ምንም ይሁን ምን ማጠንጠኛው ይከተሉት የነበረ የፍልስፍና ስርዓት ነው። በመሆኑም ኣፄ ሃ/ስላሴ ሆኑ ሌሎች ኣፄዋውያን ይከተሉት የነበረ ፍልስፍና ግልፅና የማያሻማ መሆኑን በ 1955 (እንደ ኣውሮፓ

አቆጣጠር ) በወጣው ህገ መንግስት ላይ ማንነታቸውን በግልፅ አስፍረዋል። ከዚህ በተጨማሪ የምንረዳው ነገር፣ የአፄዎቹ ብስለት በማታለልና በማጭበርበር ላይ የተመሰረተ እንደነበር በህገ መንግስታቸው ላይ የነበረአውን እንመልከት። "**እኔ በፈጣሪ አምላክ የተመረጥኩ የኢትዮጵያ ንጉስ ነኝ**" የሚለውን ሃረግ ብንወስድ በቂ ማስረጃ ነው። በእርግጠኝነት እነሱም ያውቃሉ እኛም እንረደዋለን እግዚአብሄር ኑ እናንተ የኢትዮጵያ ንጉስ ሁኑ ብሎ አልሾማቸውም፣ በጭራሽ ከነ አካቴው አለነጋገራቸውም ብዬ አስባሎህ። ነገር ግን አጭበርብረውና አታልለው ስልጣናቸው ከሃማኖት ጋር በማቁራኘት የኢትዮጵያን ህዝብ ፍዳ ያሳዩ አፄዋውያን ነበሩ ብንል ማጋነን አይሆንም ። ከዚያም አልፎ በእርስ በርስ ጦርነት እንድንማቅቅ መንገድ አበጁልን።

ለእነዚህ አረመኔ የሆኑ አፄዋውያን፣ የአማራ ገዢ መደብ፣ ነፍጠኛ፣ ዘረኛ ወዘተ ብለን ብንሰይማቸው አቄለጻጸስናቸው እንጂ አልረገምናቸውም ብዬ አስባሎህ። ምክንያቱም እውቀቱ የሌለን ሁኖ ሳይሆን ፣

- ከአለም በኢኮኖሚ ጭራ የሆነችው አገራችን በአፄዎች ደካማ መስተዳድር ነበር ማለት እንችላለን
- ከአለም በዴሞክራሲ ጭራ የሆነችው አገራችን በአፄዎች ዘረኛና መሰሬ አስተሳሰብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል
- በእርስ በርስ ጦርነት የተሰቃየነው በአፄዎቹ ደካማ አስተሳሰብና በፈጠሩት ክፍተት መሆኑን መገንዘብ እንችላለን

በመሆኑም እንደ አገርም እንደ ህዝብም እኛ ኢትዮጵያውያን (ብሄር ብሄረ ሰቦች) ተጎድተናል፣ ደምተናል፣ ተጎሳቁለናል ብዬ አስባሎህ። ግልፅ መሆን አለበት ብዬ እማስበው፣ ከአፄዎቹ ስራ በመነሳት ገዢ መደብ፣ ወዘተ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው እንጂ ከአማራነትና ከአማራ ጭቁን ህዝብ ምንም ግንኙነት እንደሌለው መገንዘብ ያስፈልጋል ።

በጣም የሚገርመው አሁንም ከጉያችን አልወጡም። "አማራ" የምትለውን ቃል በመውሰድ ከአማራ ህዝብ ለማያያዝ ይሞክራሉ ። አንዳንዱ እየመሰለውም ከጎናቸው የሚሰለፍ ህዝብ ቀላል ቁጥር ነው ብዬ አላስብም። ስለዚህ የአጼዎች የማጭበርበርና ጭካኔያቸው ከተረዳንና አገራችንም ወደ ኋላ ያስቀሩዋት መሆኑን ከተግባባን ስያሜው ለነሱና ለነሱ ብቻ ማያያዝ አለብን ብዬ አስባሎህ።

ስለዚህ ከዴሞክራሲ አንፃር ሲታይ አፄዋውያን ከእግዚአብሄር በታች ሁሉም ነገር ማድረግ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን በሃይማኖት ስም ለ700 ዓመታት ያክል የሂሊና እስረኛ ሁኖ ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም።

## 2. በደርግ ስርዓት የነበረው የዴሞክራሲ ባህልና ጉዞ

በ66ቱ የህዝብ አመፅ ይስተጋቡ ከነበሩ ቁንጮ የሆኑ መፈክሮች መካከል "መሬት ለአራሹ " እንደነበር ይታወሳል። በእርግጥ መሬት ላራሹ በደርጋውያን ግዜ በአዋጅ አስነግረዋል፣ በመረት ላራሹ ይነሳ የነበረውን ጥያቄ ለመመለስ ሞክረዋል። ነገር ግን ደርጋውያን በትረ ስልጣን እንደጨበጡ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ፣ በቡድን ሁነህ መሄድ/መጫወት ወዘተ በአዋጅ አገዱ። ያለ ህጋዊ የፍርድ ቤት ወሳኔ በየስርቻው እና በየመንገዱ ሰውን ያህል ፍጡር ይገድሉ ነበር ። ለምሳሌ

- በሃ/ስላሴ መንግስት ባለስልጣናት የነበሩ ሰዎች ያለምንም የፍርድ ቤት ሂደት ረሸንዋቸው

- **“ቀይ ሽብር በሚባል አዋጃቸው”** በኢትዮጵያ በሁሉም አካባቢ (ያለምንም የፍርድ ቤት ህጋዊ ውሳኔ) በቀበሌ ካድሬ ውሳኔ ብቻ ሰውን ያህል ፍጡር ይገድሉ ነበር።

ወጣቱ/ሰዉ የሚገደለው ለተቃውሞ አደባባይ ስለ ወጣ፣ ድንጋይ ስለወረወረ አይደለም ። ደርጋውያን እንዲሁ ከመሬት በመነሳትና ተኝተው ያለሙትን በማስታወስ እሱ/እስዋ/ ኢህአፓ ወይም የሌላ ድርጅት አባል ሊሆን/ልትሆን ይችላል/ትችላለች በሚል አመክንዮ ከየቤቱ ወይም ከየመንገዱ በመሰብሰብ በየአደባባዩ መግድል ለደርጋውያን ህጋዊ መብት ነበር ብል ማጋነን አይሆንም። ይህንን ለመገንዘብ አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ያለው የሰማእታት ሙዜም መጎብኘት ይበቃል።

በተለይ በትግራይ ተወላጆች ላይ የነበረው ግፍ እጅግ የከፋ እንደነበር “ ኢትዮጵያን የሚያስተዳድረው ማነው ?“ በሚል ርእስ በ 24/05/2017 እና “ኢትዮጵያና የዘረኝነት ልክፍት” በሚል ርእስ በ 09/06/2017 ማስረጃዎችን በማጣቀስ በአይጋ ፎሮም ፖስት የተደረገውን ማንበብ ይቻላል ።

ልክ እንደ አፄዎቹ፣ ደርጋውያን ይመሩበት የነበረ ህገ መንግስት (1988 እንደአውሮፓ አቆጣጠር ) የሚያጠነጥነው ስለ ኢትዮጵያውያን ብሄሮች፣ ብህሄረ ሰቦች እና ህዝቦች መብት አልነበረም። ይልቁንስ ዋና ማጠንጠኛው በግዛት አንድነትና በሶሻሊስት ርእዮተ ኣለም ነበር ። በዋናነት የእናውቅልሃለን የሚል አስተሳሰብ በመያዝ ሁሌ እነሱ ስለ ኣገር ኣሳቢ፣ ተቆርቋሪ መስለው ይቀርቡ ነበር። እንዲህ ኣይነት ኣስተሳሰብ የሚመነጨው ራስን ኣግዝፎ ከማየት ኣባዜ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም ከነሱ ኣስተሳሰብ ውጭ የሆነውን ሁሉ ኣገር የሚያፈርስ፣ ህዝብ የማይወክል፣ ገንጣይ፣ አስገንጣይ ወዘተ ብለው ይፈርጇሉ ራሳቸውም በዚያው መንገድ ያስባሉ ፣ ይገነዘባሉ። እነዚህ የተቀፅላ ስያሜዎች ለተለያዩ ነፃ ኣውጪ ድርጅቶች ታርጋ ተለጠፉባቸው እንደነበር ይታወሳል።

ደርጋውያን ስለ ህዝብ መብትና ተጠቃሚነት ምንም ደንታ አልነበራቸውም ብንል ማጋነን ኣይሆንም። ቢሆን ኑሮማ በገበያ ላይ የነበረውን የሃውዜን ህዝብ በኣውሮፕላን ባልጨፈጨፉ ነበር።ኣንዳንዴ ከሚናገሩዋቸው ሃረጎች ብናይ መልካም ነው። ደርጋውያን **“ቀይ ባህር የሌላት ኢትዮጵያ ማለት ኣንገት የሌለው ሰው ማለት ነው ይሉ ነበር ”**። ይህንን የደርጋውያን ኣስተሳሰብ ስኮንን፣ እንደ ዜጋ ለኣንድ ኣገር ወደብ(የባህር በር) ኣያስፈልግም ከሚል መነሻ ሃሳብ ኣይድለም ። ስለ ኣገር ስናስብ ስለ ህዝብ ማሰብ ያስፍልጋል ከሚል እሳቤ ነው። ነገር ግን ደርጋውያን ከኣፄዎቹ የወረሱት ኣስተሳሰብ ቢኖር የተለያዩ ኣስተሳሰብ የማስተናገድ ፍላጎትም ኣቅምም ኣልነበራቸውም ብንል ማጋነን ኣይሆንም። ህዝብ ካልያዝን (ህዝብ ከጎናችን ካላሰለፍን) ያለህዝብ ኣገር የሚባል ነገር ኣይኖርም ብዬ እወስዳሎህ። ስለዚህ ለኤርትራ መገንጠል ከመነሻው ለጣልያን በመሸጥ ጀምሮ እስከመገንጠልዋ ደረስ ዋና ዋና ተዋናዮች ኣፄዎች ናቸው ብዬ ኣስባሎህ። ለምን ቢባል ኤርትራን ከፌዴሬሽን ኣስተዳደር ወደ ንጉሳዊ የዘውግ ኣስተዳደር እንድትገባ ኣደረጉ። ነገር ግን የኤርትራ ህዝቦች ለመለኮታዊ የዘውግ ኣገዛዝ ተንበርካኪ ለመሆን ጭንቅላት ኣልነበራቸውም። በመሆኑም የነፃንት ትግል ማካሄድ ግድ ነበረና የኤርትራን የነፃነት ትግል የተጀመረው ልክ የኤርትራ የፌዴሬሽን ኣስተዳደር ውድቅ ከተደረገ በኋላ ነው። ስለዚህ ህዝብ ሳትይዝ የባህር በር መፈለግ ከንቱ ምኞት ሁኖ ቀረ። ላይሆንላቸው፣ በዚህ ኣስተሳሰባቸው የተነሳ ኢትዮጵያን ወደ ከፋ የእርስ በርስ ጦርነት ማቅ ውስጥ እንድትገባ ኣደረጉ።

ደርጋውያን በትምህርት፣ በቋንቋ፣ በአስተዳደር፣ ወዘተ ከአፄዎቹ የተለዩ አልነበሩም። ልክ እንደ አፄዎቹ፣ እኔ ያልኩት ትክክል ነው የሚል አባዜ ነበራቸው ። ከዚህ በተጨማሪ ደርጋውያን የወታደር ስብስብ በመሆናቸው በስነ ሃሳብ ሳይሆን በጉልበት ነበር የሚያምኑ ። ለምሳሌ ደም የሞላ ጠርሙዝን ወርወረው ደሙን መሬት ላይ እንዲዋጅ በማድረግ እኛን የሚቃወም ሁሉ ደሙን እንደዚህ እንዲፈስ እናደርገዋለን በማለት በአደባባይና በህዝብ ፊት እያቅራሩ ያሳዩን ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ ደርጋውያን (መንግስቱ ሃ/ማርያም ) ካሉት ልጥቀስ

- **በትግራይ የመንግስት ኣንድ ትራክተር የለም ብለው ተናግረው እንደ ነበር እናስታውሳለን**

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው በትግራይ ፋብሪካ ይቅርና ኣንድ የመንግስት ትራክተር እንኳን የለንም የሚለውን ሃሳብ ለማስጨበጥ የታቀደ ይመስላል። መንግስቱ ሃ/ማሪያም የተናገሩትን ስህተት ነው ብዬ ኣልወስድም። ምክንያቱም እውነታቸው ነበር ። በመሆኑም በትግራይ የትጥቅ ትግል ለማቀጣጠል ምክንያት የሆነው ይህን የመሰለ ግልፅ ኣድልዎ፣ ራስን የማስተዳደር መብት ከሚል ሃሳብ የመነጨና መብትን ለማስከበር ከመታገል ውጭ ሌላ ኣማራጭ እንዳልነበረ ያሳያል።

መታወቅ ያለበት ደርግን በህወሓትና በኢትዮጵያ ህዝቦች የተሸነፈው በማጭበርበር ኣይደለም ። ኣላማቸው በግልፅ ኣስቀምጠው ከኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች በመወያዬትና በመረዳዳት ደርግን ወደ መቃብር እንዲወርዱ ያደረጉት። ለማነፃፀር ያመች ዘንድ በመጀመርያ ኣካባቢ በደርጋውያንና በነፃነት ተዋጊ ሃይሎች (ህወሓት) የነበረው ቁመና በሚከተለው ሰንጠረዥ ሰፍረዋል

| ተ.ቁ | ማነፃፀርያ | የደርግ ወታደሮች | የህወሓት ወይም የነፃነት ተዋጊ ሃይሎች |
|---|---|---|---|
| 1 | የጦር መሳርያ | ከጦር ኣውሮፕላን ጀምሮ በዘመናዊ መሳርያ የተደራጀ እንዲሁም ከኣፍሪካ በቀዳሚ ተርታ የሚሰለፍ ነበር | ከ10 የማይበልጡ ቀላል መሳሪያዎ ነበሩ |
| 2 | የወታደር ዝግጅት | ከ3000000 የሰለጠኑ ወታደሮች የነበሩት | 10 የማይሆኑ ያልሰለጠኑ ኣባላት ነበሩዋቸው |
| 3 | ኢኮኖሚ | የኣገሪቱ ሃብት የተቆጣጠረ፣ እንደ ኣገር ከሌሎች ኣገራት መበደርና መሸመት የሚችል ሃይል ያለው | ከኣላማቸው ውጭ ምንም ነገር ኣልነበራቸውም |
| 4 | ወታደራዊ ደመወዝ | ነበራቸው | ደመወዛቸው ኣላማ ነበር |

በሰንጠረዡ የምናየው ልዩነት እጅግ የማይመጣጠን ነው። በመሆኑም የነፃነት ተዋጊዎች በትግራይ ህዝብና በኣጠቃላይ በኢትዮጵያ ህዝብ ይደርስ የነበረው ድህነት፣ ግፍ ፣ ጭቆ ፣ ራስን የማስተዳደር መብት ማጣት ወዘተ ስለኣንገሸገሻቸው እንጂ ሁኔታዎች ኣልጋ በኣልጋ ኣለመሆናቸው ከሰንጠረዡ መገንዘብ ይቻላል። ማለትም የነፃነት ተዋጊዎች ምንም ሳይኖራቸው ኣላማን ሰንቀው፣ ኣላማን ታጥቀው እልህ ኣስጨራሽ ወደ ሆነው የትግል ምእራፍ የገቡ መሆናቸው መገንዘብ ይቻላል። በዚህ የትግል ምእራፍ የተከፈለው ከ 60000 በላይ የህይወት መስዋእትነት ከ 100000 በላይ ደግሞ ቁስለኛ መሆኑን በተለያዩ ሚድያዎች ተገልፀዋል። ከዚህ በተጨማሪ የደርግ ወታደሮች የትግራይን ሃብት ከየቤቱ ዘርፈዋል፣ ኣቃጥለዋል ወዘተ።

በአጠቃላይ በአፄዎችና በደርጋውያን ለይስሙላ እንኳን ያህል የዲሞክራሲያዊ ነፀብራቅ አልነበረም ብንል ማጋነን አይሆንም። በተቃራኒ ደግሞ ለደርጋውያን የተሰጠው መብት ወሰን አልነበረውም። ምክንያቱም ያለ ህጋዊ የፍ/ቤት ወሳኔ ህብረተሰባችን (ሰውን ያህል ፍጡር) በቀበሌ ካድሬ ውሳኔ ብቻ የሞት ፅዋ ይጎነጭ እንደነበር የቅርብ ግዜ ትዝታችን ነው።

## 3. ከአፄዋውያንና ከደርጋውያን መሳለል ያልወጣ ትርክት

አሁንም ቢሆን ከአፄዎችና ደርጋውያን አስተሳሰብ ያልወጣ ትርክት በማህበራዊ ሚድያ፣ በሬድዮ፣ በተለኤቭዥን ሲሰራችጭ እንመለከታለን። ከፅሁፋቸው ይዘት ሲታይ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩት ሃይሎች፣

- የአማራ ተውላጆች የሁኑና ፅንፈኛ አቅዋም ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ናቸው

ፅንፈኞቹ ልክ እንደ አያቶቻቸው ስለ ኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች ደንታ የላቸውም። በተለይ በዘሃበሻ ድህረ ግፅ ላይ በአማራ ብሄርተኝነት የሚውተረተር ዘገባ ይደመጣል። በዴሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት ማእበል ውስጥ ቢሆን መልካም ነበር። ነገር ግን ሀ ብለው ሲጀምሩ " የአማራ ብሄርተኝነት ማለት ኢትዮጵያዊነት" ብለው ይዳክራሉ። በሌላ መልኩ ደግሞ ከአማራ ውጭ የሆነውን ሁሉ በጎሳ ይፈርጃሉ። ማለትም የኦሮሞ፣ የትግራይ ወዘተ የሆነውን ህዝብ ሁሉ ከጎሳ የዘለለ ስም ሲሰጡት አይታይም። ስለ ብሄርና ጎሳ ያላቸው ልዩነት በሌላ ቀን እመለስበታሎህ።

ከዚህ በተጨማሪ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ከክቡር የቀድሞ ጠቅላይ ሚንስተር አቶ መለስ ዜናዊ ሲወያዩ "አማራ የሚባል ህዝብ የለም " ሲሉ አዳምጫሎህ። የፕሮፌሰሩ ንግግር እዚህ መጥቀስ ያስፈለገበት ምክንያት አማራ የሚባል ህዝብ ከሌለ አማራ በጎሳ ደረጃ ሊመደብ የሚችል እንዳልሆነ ስለሚያሳዬን ነው። ስለዚህ "የአማራ ብሄርተኝነት ማለት ኢትዮጵያዊነት" የሚለው የምንወስድ ከሆነ ኢትዮጵያን በሙሉ የአማራ ነው ለማለት የተፈለገ ይመስላል። በነሱ አነጋገር ከአማራ ውጭ የሆነውን ሁሉ በጎሳ የሚፈረጅ ከሆነ እንዴት የአማራ ቤሄርተኝነት ኢትዮጵያዊነት ሊሆን ይችላል? ከአገላለፃቸው እንደምንረዳው ከሆነ አሁንም "አንድ አገር አንድ ህዝብ" የሚለው የደርጋውያንና የአጼዋውያን ትምክህት፣ ዘረኝነት ወዘተ የሆነውን አስተሳሰብ አምቀው መያዛቸው ያሳያል።

የዚህ ቡድን አንቀሳቃሾች በሚያራግቡት አስተሳሰብ ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍል ማስከተል መቻላቸው መገንዝብ የምንችል ይመስለኛል። ለማሳያነት ያክል በጎንደርና በምእራብ ጎጃም ተከሰቶ የነበረው አመፅ ማየት በቂ ነው። ልክ እንደአፄዎቹ ስለ ህዝብ ማንነትና ደህንነት ዴንታ የላቸውም ብዬ በድፍረት መናገር እችላሎህ። ለምሳሌ በ2008 ዓ/ም በጎንደርና በምእራብ ጎጃም የተቀሰቀሰውን አመፅና መዘዙ በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል። እጅግ የከፉ ፀረ ህዝብ እንቅስቃሴ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህ አመፅ ላይ፣

- የአፄዎቹ /ደርጋውያን ሉሙጥ ባንዴራ ይዘው ነበር ፉከራቸው ያስተጋቡት ፣
- ብሄርን (ዘርን) ማእከል አድርገው የአፄዎች/ደርጋውያንን የተለመደ ባህርይ በቅማንትና በትግራይ ተወላጆች ግፍ መፈፀማቸው ይታወሳል፣
- የይሁኔ በላይ ዘፈንን እጠቅሳሎህ " ማንነቴ መልሱ እያለ ሲዘምር ዋለ. . . ." ብሎ እንዳረጋገጠው በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል።

በኣመፀኛቹ ጥቃት ኣማካኝነት

- ከ 11000 በላይ የትግራይ ተወላጆች ተፈናቅለዋል
- የትግራይና የቅማንት ተወላጆች የሆነውን ሃብትና ንብረት ተዘርፈዋል/ተቃጥለዋልም
- ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ የትግራይ ተውላጆች ህይወታቸው ኣጥተዋል

ይህንን በተመለከተ "ኢትዮጵያን የሚያስተዳድረው ማነው ?" በሚል ርእስ በ 24/05/2017 ገፅ 9 ላይ እና "ኢትዮጵያና የዘረኝነት ልክፍት" በሚል ርእስ በ 09/06/2017 ገፅ 20 ላይ ማስረጃዎችን በማጣቀስ በኣይጋ ፎሮም ፖስት የተደረገውን ማንበብ ይቻላል ።

ከዚህ በተጨማሪ በወልቃይት ያለው ህዝብ ምንም ይሁን ምን ሳያመዛዝኑ "ተከዜ ምላሽ ኣማራ ነው" ብለው በማሰብ "ትግሬ እንጂ ትግራይ ተከዜ ተሻግሮ ኣያውቅም" በማለት ጎንደር ሁነው ስለ ወልቃይት ሲያቅራሩ ታይተዋል። ኣንድ ነገር ትዝ ኣለኝ፣ ደርጋውያንና ኣፄዋውያን ያቅራሩበት የነበረውን ላስታውስችሁ " ድንበራችን ቀይ ባህር ነው " ይሉ ነበር ። ኣሁን ድንበራቸው ወደ ተከዜ ማፈግፈጉ ኣንድ ጉዳይ ሁኖ እምነታቸውና ኣስተሳሰባቸው ግን ህዝብን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ እንዲሁ በስሜት መሪትን የመጠቅለል ዝንባሌ ባህርያቸው በግልፅ ኣሳይተዋል። ስለዚህ ይህ ዓይነት ኣስተሳሰብ ከደርግና ከኣፄዎች ያላቸው ዝምድና ለማስተሳሰር ይቻላል ብዬ ኣስባሎህ።

ኣሁንም ልክ እንደ ደርጋውያንና ኣፄዋውያን የትግራይ ህዝብ ከሌላ ጭቁን የኣማራ ህዝቦች ለመነጠል (የኣማራና የትግራይ ህዝብ ) ለማለያዬት የማይሉት ነገር የለም። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ፣

- " የትግራይ የበልላይነት" ፣ "የወያኔ መንግስት" ፣ የወያኔ ሰራዊት፣ ወዘተ ሌላውን ህዝብ እንደፈለገ እያደረገ ነው ይላሉ
- ትግራይ በእንዱስትሪ ልትሰምጥ ናት የሚል ሃሳብ ያናፍሳሉ ፣ በተለይ ዘሃበሻ በሚባለው ድህረ ግፅ

የትግራይ የበላይነት የሚለው በእያንዳንዱ ክልል ያለው ህዝብ በማን እንደሚስተዳደር ያውቀዋል ብዬ ኣስባሎህ ። ከዚህ በተጨማሪ የኣማራን ህዝብ በተመለከተ በህዝብ ተውካዮች ም/ቤት ያለው ውክልና በሰንጠረዥ 2 ይመልከቱ። እንዲሁም በፌዴራልና በክልል ያለው የመንግስት ኣወቃቀር ስልጣን በተመለከተ "ኢትዮጵያን የሚያስተዳድረው ማነው ?" በሚል ርእስ በ 24/05/2017 እና " ኢትዮጵያና የዘረኝነት ልክፍት" በሚል ርእስ በ9/06/2017 በኣይጋ ፎረም ፖስት ተደርገዋል ማንበብ ይቻላል። በኣጠቃላይ ግን በኣሁኑ በእያንዳንዱ ክልል የሚኖረው ህዝብ በማን እየተስተዳደረ እንዳለ ለመወሰን ፍርዱ ለየክልሉ ህዝብ ቢሆን የተመረጠ ነው እላሎህ። ከዚህ በተጨማሬ በኣሁኑ ሰዓት ኣንድ ብሄር በሌላው ጣልቃ ገብቶ ለመፈትፈት የሚያስችል/የሚፈቅድ ህግ የለም በኣሁኗ ኢትዮጵያ። እንዲሁም በኢትዮጵያ ካሉት ክልሎች ውስጥ ኣንዱ መድልዎ ደርሶብኛልና ኣይመቸኝም የሚል ከሆነ ከመደራደር ኣልፎ በቃኝ ብሎ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን ስልጣን (እስከ መገንጠል ድረስ) የሚያስችለው የህግ ማእቀፍ ኣለ ። ስለዚህ የሚነዛው ወሬ ከበሬ ወለደ ከሚባለው ነገር የዘለለ ኣይደለም።

**እዚህ ላይ ለመግልፅ የምፈልገው ነገር ግን " የኣባዬን እከክ ለእምዬን ነከክ" እንደሚባለው የሚያወሩት ወሪ ምናልባት እነሱ ራሳቸው እድሉን ቢያገኙ መስራት የሚፈልጉትን ይሆናል ብዬ ኣስባሎህ ።**

ትግራይ በእንዱስትሪ ልትሰጥም ናት ተብሎ የሚናፈሰው ወሪም ኣለ። ትክክል ቢሆን ኣያሳፍርም ደስ ሊላችሁና ሊለን በተገባ ነበር ። የመልማት ጉዳይ ለትግራይ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ክልል ኣካባቢው የማልማት ስልጣን ኣለውና። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በትግል ወቅት የነበረው ቁንጮ ሃሳብ የትግራይ ህዝብና ሌላው የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች

- የመስራት ነፃነት ኣጣን፣
- ኣውርቶ ሳይሆን ሰርቶ የመበልፀግን መብት ኣጣን
- ብሄራዊ ጭቆና መሸከም ኣልቻልንም የሚሉ ነበሩና

በውሸት ናዳ ግን ልታደነቁርን ግን ኣይገባም እላሎህ። ምናልባት ያልተገባ እላፊ የሚባል ነገር ካለና ከነማስረጃው ከቀረበ ፣ የትግራይ ህዝብና መሪ ድርጅቱ ራሳቸው በራሳቸው ስህተታቸው የማረም ኣቅምና ቁመና ያላቸው ናቸው ብዬ ኣስባሎህ። የማይመለከታቸው ኣይፈልጉምም፣ ፈልገውም ኣያውቅም።

በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ እንደ ኣፄዎቹና ደርጋውያን (መንግስቱ ሃይለማርያም) **በትግራይ " ኣንድ የመንግስት ትራክተር እንዳይኖር ፣ ሃብት እንዳይፈራ፣ ዝም ብላችሁ ድሃ ሁኑ** በሚለው ኣስተሳሰብ ለመቀጠል ተፈልጎ ከሆነ የትግራይ ህዝብ እንደህዝብ እና በዚህ ስርዓት ራሳቸው በራሳቸው የማስተዳደር መብት ያገኙ ህዝቦች ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል ። ስለዚህ መልሱ ለትግራይ ህዝብናራሳቸው በራሳቸው የማስተዳደር መብት ያገኙ ህዝቦች ልተወው።

ከዚህ በተጨማሪ **በትካል እግሪ ምትካል ትግራይ** (ትእምት) እንቅስቃሴ ኣይናቸው ደም የሚያሾራቸው ኣሉ። በኣንድ በኩል ትግራይ በእንዱስትሪ ልትሰጥም ናት ምነው ዝም ኣላችሁ የሚል መልእክት ያስተላልፋሉ በሌላ መልኩ ደግሞ ከትእምት የትግራይ ህዝብ ተጠቃሚ ኣይድለም ለማለት ይከጅላሉ። ከዚህ ፅንሰ ሃሳብ የምንረዳው ቁልፍ ተግባራቸው ትእምት ለማምከን የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች መሆናቸውን ነው። ነገር ግን እንዴት ነው የትእምት ህልውና ጥያቄ ውስጥ ኣስገብተው ስለ ተጠቃሚነት ማውራት የሚቻለው። በፍፁም ኣይቻልም። የወሪያቸው ፍሰት እርሱ በእርሱ የሚጋጭ ነው የሚመስለኝ። ስለ የትግራይ ህዝብ ተጠቅሚነት የምናወራ ከሆነ ከሁሉ በፊት የትእምት ሲረጋገጥ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ነገር ትእምትን ኣጥፍተህ እንዴት በሌለ ነገር ስለ ተጠቃሚነት መነጋገር የሚቻለው?

በኣሁኑ ሰዓት ከኦሮምያ መንግስት የሚያስደስት ዜና እየሰማሁኝ ነው ፣ የኦሮሞ ህዝብ ካልሰራና ካልበለፀገ እንዲሁም ካልተማረ ምንግዜም ቢሆን ከጫና መውጣት ኣይችልም ብለዋል የኦሮሞ መንግስት ኣመራሮች። የኣረንጓዴ ኣብዮትም ኣውጀዋል። ትክክል ናቸው። ምክንያቱም የኦሮምያ መንግስት ለመስራትና ለመበልፀግ ያላቻው ተነሳሽነት ያሳያል። በዚህ መልኩ የሚቀርብ ልማታዊ ኣስተሳሰብ ለሁላችንም መልካም ነው። ነገር ግን ቁጭ ብለው በሌላ ላብ ለመበልፀግ የሚፈልጉ ሃይሎችና ቅናታሞች የሆኑ ሰዎች ግን ቢቃን ልንላቸው ይገባል። ንግግራቸው/ ፁሁፋቸው በጣም ነው የሰለቸን ። ሁሉ ግዜ እነሱ ወደ ቆሙበት ጭቃ ሊያወርዱን ይፈልጋሉና ቦታ ልንሰጣቸው ኣይገባም እላሎህ።

**እዚህ ላይ ላሰምርበት የምፈልገው የኦሮምያ የመንግስት ኣመራሮች የተከተሉትን ፈለግ ሁሉም ክልሎች እንደየኣቅማቸው ቢከተሉት ለኣጠቃላይ ኣገራዊ እድገት ትልቅ ፋይዳ ኣለው እላሎህ።**

## 4. በኢህዴግ ስርዓት የዴሞክራሲ ባህልና ጉዞ

ኢህዴግ የደርግን ሰራዊት ደምስሶ ኣዲስ ኣበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ብቻውን የመንግስትነት ተቅዋም ኣልመሰረተም። ይልቁንስ የዘላቂ ሰላም ታሳቢ በማድረግ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ኣስፈላጊነት ተገነዘበ። በመሆኑም በሰላምዊ የትግል ማእቀፍ ውስጥ ገብቼ እታገላሎሁ የሚል ወገን ሁሉ (ኣዲስም ሆነ ነባር ፖለቲካ ፓርቲ) በሽግግር መንግስት እንዲሳተፉ ጥሪ ኣቀረበ። በጥሪው መሰረትም አነግን ጨምሮ ከሃያ በላይ የተለያዬ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ታዋቂ ግለ ሰቦች ፣ የህብረተ ሰብ ወኪሎች የተሳተፉበት የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ቻርተር ለማፅደቅ ተሰባብሰቡ። በዚህም መሰረት፣

> **በኢትዮጵያ ለመጀመርያ ግዜ የተለያዬ ኣመለካከት ያላቸው ፓርቲዎች፣ የህብረተ ሰብ ወኪሎች ወዘተ ባሉበት በጋራ ተወያይተው በሽግግር ወቅት የሚተዳደሩበት ቻርተር ማፅደቅ ቻሉ (1991) ። ስለዚህ በኢትዮጵያ ለመጀመርያ ግዜ የዴሞክራሲ ፋና ወጊ የሆነና የዴሞክራሲ መርህ የተከተለ ፍፃሜ ነው ብንል ማጋነን ኣይሆንም።**

በጉባኤው የፀደቀው ቻርተር በሽግግሩ ወቅት የህጎች የበላይ ህግ ሁኖ እንዲያገለግል ተወሰነ። ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት ዴሞክራሲ ማለት ሁሉም ባሻው መንገድ መጓዝ ማለት ሳይሆን የፖለቲካ ድርጅቶች ፣ሲብል ማህበራት፣ የእምነት ተቅዋማት ፣ ግለ ሰቦች ወዘተ በህግና በስዓርት መብቶቻቸውን ማስጠበቅ ለማስቻል እንደሆነ እንረዳለን።

በኣገሪቱ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ስልጣን እስኪረከብ ድረስ በሽግግሩ ወቅት ሁለት ም/ቤቶች እንዲኖሩ በሽግግሩ መንግስት ቻርተር በግልፅ ሰፍረዋል። እነሱም የተወካዮች ም/ቤትና የሚንስትሮቸ ም/ቤት ናቸው። የተወካዮች ም/ቤት ከፖለቲካ ድርጅቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ከነፃነት ንቅናቄዎች ሁኖ ከ 87 ኣባላት በማይበልጥ እንዲመሰረት ተወሰነ። ከ 87 መቀመጫዎች መካከል ኢሃዴግ 32 ወንበሮች የያዘ ሲሆን 55 መቀመጫዎች ደግሞ በሌሎች የፖሊቲካ ድርጅቶች፣ የነፃነት ንቅናቄዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ ነበር በም/ቤቱ የተወከሉ ። የተውካዮች ም/ቤት ቻርተሩ መሰረት ኣድርጎ ኣዋጆችን ያፀድቃል፣በጀት ያፀድቃል፣ ከመንግስት ተፅእኖ ነፃ ፍ/ቤቶች ያቋቋማል፣ የሚኒስትሮች ሹመት ያፀድቃል ወዘተ። በኣጠቃላይ የተውካዮች ም/ቤት ኣጠቃላይ የመንግስት እንቅስቃሴ በበላይነት እንዲመራ ቻርተሩ በግልፅ ኣስቀምጠዋል። ከዚህ በተጨማሪ የብሄሮች ኣሰፋፈር መሰረት ኣድርጎ የክልልና የኣካባቢ ምርጫ በተቻለ መጠን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲካሄድ ያትታል (ለዝርዝር መረጃ የኢትዮጵያ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የሽግግር መንግስት 1983 ዓ/ም መመልከት ይቻላል) ። በሽግግሩ ቻርተር ውስጥ ከተካተቱት መካከል ፣

- "የእምነት፣ ሃስብን የመግለፅ ፣የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብና የመቃወም መብት"
- "የሌሎችን ህጋዊ መብቶች እስካልተጋፉ ድረስ በማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላኣንዳች ገደብ የመሳተፍ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች የማደራጀት መብት " (1991 እንደ ኣውሮፓ ኣቆጣጠር)

የሽግግር መንግስት የኣገሪቱን ህገ መንግስት ኣርቃቂ ኮሚሽን በመሰየም የኢትዮጵያ ፌዳራላዊ ዴሞክርስያዊ ሪፓፐሊክ ህገ መንግስት በህዝብ ተሳትፎ ኣፀደቀ። በህገ መንግስቱ ማርቀቅ ስራ ተስማርተው ከነበሩት መካከል ኣንዳዶቹ እንደገለፁት በእያንዳዱ ኣንቀፅ የህዝብ ውይይት ተደርጎ በመጨረሻም የህዝቡን ኣብላጫ ድምፅ መሰረት ተደርጎ እንደተቀረፀና እንደፀደቀ በቅርቡ በኢትዮጵያ ብሮድ ካስት ኮርፖሬሽን መስኮት ቀርበው ምስክርነታቸው ሰጥተዋል ።

ከዚህ በተጨማሪ በንፁህ ልቦና ካየነው የቅርብ ግዜ ስራ በመሆኑ በህገ መንግስት ውይይት የተሳተፉ ሰዎችን በመጠየቅ መረዳት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት የቡድን፣ የግል፣ የሃማኖት፣ አለማቀፍ ሰባዊ መብቶች እንዲከበሩ ያስቀምጣል። ፍፁም ነው ባንልም፣ በህገ መንግስቱ የሰፈሩ መብቶች ጥግ ድረስ የሄዱ የዴሞክራስያዊ መብቶች ኣሉ ብንል ማጋነን ኣይሆንም። ከነዚህ መካከል።

- **ራስ የማስተዳደር መብት በተመለከተ፣** እንደሚታወቀው የክልሎች ኣመሰራረት በቋንቋ ነው ብንል ማጋነን ኣይሆንም። በመሆኑም በበለጠ ለመደራጀትና የሚወክሉትን ማህበረሰብ ጥቅም ለማስከበር ይቻል ዘንድ የመደራደር ኣቅማቸው ያጎለብታል ተብሎ ይታመናል። ከዚህ በተጨማሪ መብቴ ተረገጠ፣ ጭቆና በዝቶብኛል፣ የሚል ክልል ካለ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን ስልጣን እስከ ነፃነት ድረስ መብት እንዳለው በግልፅ ያትታል። የዚህ መብት ትርጉሙ የኣገርን ኣንድነት የሁሉም ሰው ፍቃድ የሚጠይቅ እንጂ ግለ ሰቦች ከበላይ ሁነው የሚወስኑት ኣለመሆኑን ያመለክታል ። ይህ በመሆኑ፣
    - **ኣንዳንድ ሰዎች ራስ የማስተዳደር መብት ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ነው ይሉታል።** እስኪ ቆም ብለን እናስብ። የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የሚለውን ብንወስድ ብሄር፣ ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች የበለጠ የመደራጅትና የመወሰን ስልጣን ያጎናፀፈ ነው እንጂ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ኣይደለም፣ ሊሆንም ኣይችልም። እያንዳንዱ ብሄር፣ ብሄረ ሰብና ህዝቦች ራሳቸ በራሳቸው እድላቸውን የመወሰን ስልጣን መንፈግ በኣሁንዋ ኢትዮጵያ ኣይቻልም።፣ የምናስብ ካለንም የኣፄዎችና ደርጋውያን ይጠቅሙበት ወደ ነበረው ፖሊሲ እንመለስ ማለት እንደሆነ መገንዝብ ይቻላል።
    - **ኣንዳንድ ሰዎች የኣማራን ማንነት ለማጥፋት የታለመ ፖሊሲ ነው ይሉታል።** የኣማራ ብሄር ተውላጆች በኣንድ ክልል ተሰባስቦ ራሳቸው በራሳቸው ማስተዳደራቸው ፣ ባህላቸውና ማንነታቸው ማሳደጋቸው እንዴት ነው ኣማራን ለማጥፋት የተቃኘ ፖሊሲ ሊባል የሚችለው? በፍፁም ሊሆን ኣይችልም ኣባባሉ፣ ለማመንም ለማሳመንም የሚምች ኣይደለም። ምናልባት በኣማራ ስም ይነግዱ የነበሩ ሊሂቃን ሌላው ህዝብ የሚኖርበት ኣካባቢ ማለትም እንደ ትግራይ፣ ኦሮምያ፣ ሶማሊያ ወዘተ እነሱ በፈለጉት መንገድ ባለ ማስተዳደራቸው ሊቆጫቸው ይችላል። መነሻውም በነሱ ኣባባል መሬቱ ብቻ ሳይሆን ህዝቡንም የኛ ኣገልጋይ ነው ብለው ስለ ሚያምኑ ይሆናል ይህን ሃሳብ የሚያራምዱ።
- **በቋንቋህ የመማር መብት፥** በቋንቋህ የመማር መብት ዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊነትም ጭምር ነው። ስለዚህ በኣሁኑ ሰኣት ከሞላ ጎደል ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በቋንቋቸው የመማር መብት ተጎናፅፈዋል። በቀደምት ስርዓቶች ግን ሰብዓዊ መብትም በመጣስ ህፃናት ልጆች ሳይቀሩ በኣማርኛ ብቻ እንዲማሩ ይደረግ ነበር።
- **ፍትህ በተመለከተ፥** ብሄር ፣ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች በቋንቋቸው ፍትህ እንዲያገኙ ተደርገዋል። በቀድሞ ስርዓት ግን የኣስተዳደርና ፍትህ በኣማርኛ ብቻ ነበር። ኣማርኛ የማያውቁ ፋራ ተብሎ ይጠሩ ነበር።
- **ከክልል ባለፈ በኣገር ደረጃ ፍትሃዊና የተመጣጠነ ውክልና እንዲኖር ኣስችለዋል፣** ለምሳሌ የኣገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን ኣካል የሆነው የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው። በመሆኑም እያዳንዱ ብሄር፣ብሄረ

ሰቦችና ህዝቦች ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው ተደርጎ ተሰርተዋል። በዚሁ መስረት ከእያንዳንዱ ክልል የሚወከሉ የምክር ቤት አባላት በሰንጠረዡ ሰፍረዋልና ማመዛዘን ይቻላል።

ሰንጠረዥ 2. ከየክልሉ የሚውክሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የአባላት ብዛት የሚያሳይ

| | ትግራይ | ኣፋር | ኣማራ | ኦሮምያ | ቤንሻንጉል | ጋምቤላ | ሶማሊያ | ሃረሪ | ደቡብ ህዝቦች | ኣዲስ ኣበባ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 38 | 8 | 138 | 178 | 9 | 3 | 23 | 2 | 123 | 23 | 547 |
| % | 6.94 | 1.46 | 25.23 | 32.54 | 1.92 | 0.55 | 4.2 | 0.37 | 22.49 | 4.21 | 100 |

- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የፌደራል ስራ ኣስፈፃሚ ሹመትን ያፀድቃል ፣ ይቆጣተራል ፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወዘተ። ከሰንጠረዡ እንደምናየው ከትግራይ የተወከሉት ኣባላት ወደ 7% ኣካባቢ ናቸው። በምን መልኩ በ 38 (7%) ከትግራይ የተወከሉት ኣባላት ለ 547 (93%) ኣባላት ያሉት ም/ቤት የበላይነት ሊያሳዩ የሚችሉት ። ማንም ሰው ሊግነዘበው የሚችል መረጃ ነውና እያዳንዳችን ኣስተያዬት የመስጠት ሃላፊነቱ የኛ ነው እላለሁ ።

ስለዚህ የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጥግ ድረስ በመሄድ ከላይ የገለፅኳቸው ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በተግባር ለማስከበር ጥረት እየተደረገ ነው ያለው ፣ እየተሰራበትም ያለ ህግ ነው ብዬ ኣስባለሁ ። ነገር ግን በኣንዳንድ የኣማራ ተወላጆች ነን ባዮችና ሊሂቃን፣ ኣሁን ያለው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ህገ ኣራዊት ይሉታል። ወይም ደግሞ የወያኔ ፍልስፍና በመሆኑ የህወሓት የበላይነት ያሳያል ሲሉ ይደመጣሉ። የፅንሰ ሃሳቡ ወይም መርሁ ከየተኛውም ወገን ቢሆን ችግር ያለበት ኣይመስለኝም ። ነገር ግን በፅንሰ ሃሳቡ ጠቃሚነት ወይም ጎጂነት ላይ መነጋገር ይቻላል። ፅንሰ ሃሳቡ ከወደ ትግራይ ስለተወለደ ብቻ ኣያስፈልግም ወይም ደግሞ ህገ ኣራዊት ብትሉት ለራሳችሁም ቢሆን የሞራል ውድቀት ነው ብዬ ኣስባሎህ። የማን ፍልስፍና ይሆን የሚፈልጉት? ምናልባት እኛ በፈጣሪ የተሰየምን ንጉሶች ነን ይሉን ይሆን? ወይም ደግሞ የእናውቅለሃለን ብሂል ይነግሩን ይሆን? በእርግጥ ቢሉም ኣይደንቃቸውም!!!

ብናምንም ባናምንም በኣሁን ሰኣት ያለው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት የምናጣጥለው ህግ ኣይደለም። ምክንያቱ የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች ኣንኳር የሆኑ ጥያቄች የመለሰ ህገ መንግስት ነው ብዬ ኣስባሎህ። በተለይ ከቡድን መብት ኣኳያ ከሞላ ጎደል ተመልሰዋል ብንል ማጋነን ኣይሆንም። መሬት ላይ ወርዶ ስራ ላይ የማዋል ጉዳይ ግን ውስንነት እንዳለ እንመለከታለን። የውስንነቶችን ምክንያት ይሆናሉ ብዬ የማስበው

- ህብረተ ሰባችን በዴሞክራሲ ያለው ግንዛቤን እንደ ትልቅ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ኣንድ ሰው የራሱን መብት እንዲከበርለት ሲፈለግ የሌላውን መብት መንካት የለበትም። በኣጠቃላይ በህገ መንግስቱ የተቀመጡትን መርሆዎች ተከትሎ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል እላሎህ። እስከ ኣሁን ህግና ደንቡ ባለመጠበቃችን ምክንያት በኣንድ ወይም በሌላ መልኩ ዋጋ ኣስከፍሎናል። በዴሞክራሲያዊ እድገታችንም ኣሉታዊ ጫና ኣያሳድርም ለማለት ኣልደፍርም።
- በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ ግለ ሰቦችም ራሳቸውም ከህብረተሰቡ የወጡ በመሆናቸው ከቀደምት ስርዓቶች ነፀብራቅ ነፃ ናቸው ብለን መወሰድ ኣንችልም። ምክንያቱም ያደግንበት ፀረ ዴሞክራስያዊ ስርዓት ትልቅ ጋሪጣ ሂኖብናል ብዬ ኣስባሎህ።

ስለዚህ በኢህአዴግ ግዜ ያለው የዴሞክራሲ ባህልና ጉዞ በእጅጉ ከአፄዎቹ እና ደርጋውያን የተሻለ መሆኑን ደፍሪ መናገር እችላሎህ። በፍፁም አይወዳደርም እላሎህ ምክንያቱም በእያንዳንዱ የመግስታት ምእራፍ የነበረው ሁኔታ በዚህ ፅሁፍ ለማስቃኘት ተሞክረዋል። ነገር ግን ከአፄዎቹና ከደርጋውያን የመሻል ሁኔታ አንድ ነገር ሁኖ ለአሁኑ ያለው መንግስት ግን ሊያኮራው አይገባም እላሎህ። መንግስት ስለ ህገ መንግስት መርሆዎችና ድንጋጌዎች ህብረተሰቡን ማስተማርር ይጠበቅበታል ። እንዲሁም ወደ ኋላ ሳይሆን ማየት ያለበት ከሌሎች አገሮች ማነፃፀር ይገበዋል ብዬ አስባሎህ። በየጊዜው ያለው የዴሞክራሲ እድገትም መገምገምና ማስገምግም ያለበት ይመስለኛል።

በአጠቃልይ ከህብረተሰብ፣ ከመንግስት፣ ከሲቢክ ማህበራት፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች ምን ይጠበቃል ለሚለው በምርጫ 1997 ዓ/ም የነበረው ሁኔታ መሰረት አድርጌ አስተያዬት ለመስጠት ወደድኩኝ።

**ምርጫ 97፣ በ**መንግስት በኩል ስንመለከት ምርጫው ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ቁርጠኛ አቋም ይዞ መግባቱ ብዙ ማሳያዎች አሉ። ለምሳሌ የህዝቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ሲባል በፓርቲዎች መካከል ይደረግ የነበረው የምርጫ ቅስቀሳ ነፃና ግልፅ እንዲሆን ማድረጉ አብዛኛዎቻችን የምናስታውሰው ጉዳይ ነው። ውድድሩም በቴሌቭዥንና በራዲዮ የቀጥታ ስርጭት ሽፋን አግኝቶ ይተላለፍ እንደነበር ይታወሳል። ምንም አንኳን በመጨረሻ አካባቢ አንዱን ሌላውን የመነናተልና የመፈራረጅ ሁኔታዎች ቢኖሩም በወሳኝ መልኩ ስንመለከተው በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ጥሩ ትምህርት የተወሰደብት ነበር ማለት ይቻላል። እንዲሁም ምርጫው በተካሄደበት ቀንም እጅግ ሰላማዊና ህዝቡም በንቃት የተሳተፈበት እንደነበር ሁላችን የምናስታውሰው ነው።
ከምርጫው ማግስት ጀምሮ ግን ያልተጠበቀና የኢትዮጵያ የምርጫ ህገና ደንብ ያልተከተለ ስራ ተከሰተ። እንደሚታወቀው አጠቃላይ የአገሪቱ ምርጫ ውጤት መግለፅ ያለበት የምርጫ ኮሚሽን ሁኖ ሳለ፣ ቅንጅት ይባል የነበረ ፓርቲ (በነ ብርሃኑ ነጋ የሚመራ) በመላ አገሪቱ የተካሄደው ምርጫ እኔ ነኝ ያሸነፍኩ ብሎ ያለ ስልጣኑ አወጀ። የቅንጅትን አዋጅን ተከትሎ ኢህአዴግም በአዲስ አበባ ቢሸነፍም ከመላ አገሪቱ የተገኘው አጣቃላይ ውጤት ሲመዘን፣ መንግስትን ለመመስረት የሚያስችለኝ ድምፅ አግኝቻሎህ ብሎ አወጀ። ድርጊቱ የመቅደምና የመዘግዬት ካልሆነ በስተቀር ከህግ አንፃር ሲታይ ሁለቱም የፖለቲካ ድርጅቶች ትክክል አልነበሩም ማለት ይቻላል። ከዚህ በኋላ ነው የ 97 ዓ/ም ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ሂደት መልኩ እየተቀየረ የሄደው።

በእርግጥ በየተኛውም አለም ሁለት ተፎካካሪ ፓርቲዎች የመነናተተሉ ጉዳይ ያለና የነበረ ነው። ለምሳሌ በ2016 የአመሪካ ፐረዚደንታዊ ምርጫ ብንወስድ ከፍተኛ የሆነ የመነናተተል ፍጥጫ አይተናል። ትራምፐ ካሸነፉ በኋላም አመሪካውያን ትራምፐ አይውክለንም ብለው ሰልፍ ወጥተዋል። በክሊንተን በኩል ለሰልፈኞች የተሰጠ ምላሽ ግን ትራምፐ አሸንፈዋል ተረጋጉ ነው ያሉት። ነገር ግን ትራምፐ ወደ ስልጣን የመጡበት ምስጢር ግን አሁንም በህግ እየተጣራ ያለ ጉዳይ መሆኑን እየሰማን ነው። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን፣ የአመሪካውያን የዴሞክራሲ ምጥቀትና እድገት በዚህ ነው የሚገለፀው። ማለትም ህዝብን አረጋግቶ፣ ነገሮች በህግ እንዲታዩ ማድረግ እጅግ የበሰለ የዴምክራሲ ባህል መሆኑን እንገነዘባለን። ለዚህም ነው በመግብያዬ ላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ዴሞክራሲ በአንድ ጀንበር የሚሰጥ ወይም የሚነፈግ አይደለም ለማለት የፈለግኩት።

ወደ አገራችን ምርጫ 97 ለመልሳችሁ። ቅንጅት በምርጫ ኮሚሽን የሚሰጠው መግለጫ ሳይጠብቅ የአዲስ አበባን ህዝብ በመሰብሰብ የምርጫ ውጤት ተጭበርብረዋል ብሎ መስበክ ጀመረ። የስብከቱ ማጠንጠኛ ህዝቡ ውጤቱ

እንዲያከብርለት መማህፀን ነበር ተያያዘው። በዚህም መሰረት ወደ ግርግር ተገባ። ከግርግሩ ለመታቀብ ይቻል ዘንድ መንግስት ለተወሰነ ግዜ የሚቆይ የሰለማዊ ሰልፍ እገዳ ጣለ ። በኣዋጁ መሰረት ንብረት ማውደሙ፣ ብጥብጥ ወዲያውኑ ኣልቆምም። በመሆኑም በነበረው ብጥብጥ ምክንያት መክፈል ያልነበረብን የህይወት፣ የሞራልና የንብረት ዋጋ ከፈለናል።

በኣመሪካና በኣገራችን የነበረ ሁኔታ ኣወዳድሩ። በኛ ኣገር ገና ውጤት ሳይገለፅ ህዝብን ወደ ብጥብጥ መጋበዝ በኣመሪካ ደግሞ በህዝብ ቁጣ የተነሳውን ኣመፅ የማብረድ ስራ ተሰራ።

ኣሁንም ወደ ኣገራችን ልመልሳችሁ፣ ከወራት በኋላ ከኣገሪቱ ከተሰበሰበው ኣጠቃላይ የምርጫ ውጤት መንግስት ለመመስረት የሚያስችል ድምፅ ያገኘ ፓርቲ ኢህኣዴግ መሆኑን የኢትዮጵያ ምርጫ ኮሚሽን ይፋ ኣደረገ። የምርጫ ውጤት ይፋ ማድረግን ተከትሎ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ማስተናገጃ መድረክ/ ኣሰራር ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ህግ /ስርዓት ነበር። በመሆኑም ቅሬታ ያለው ፓርቲ/ግለሰብ ህጉን ተከትሎ ቅሬታውን ማቅረብ የሚቻልበት ኣግባብ ነበር ማለት ነው። ቅንጅት ብጥብጥ ከማድረግ ተቆጥቦ የህጉን ኣግባብ ተከትሎ ብሄድ ኑሮ ፣

- ህብረተሰባችን የዴሞክራሲን ባህልና ትርጉም ለመገንዘብ የሚችልበት እድል ነበር እላሎሁ
- በፍትህ ኣካላት ላይ ምንም ቢሆኑ ምንም የህሊና ጫና በመፍጠር ወደ እውነት እንዲከተሉ ማድረግ በተቻለ
- የማጭበርበር ስራ እንኳን ቢኖር ህዝቡ ራሱ በሂደት የመከላከል ኑልበቱ/ኣቅሙ ያድግ ነበር

ነገር ግን ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ራሱ ፓርቲው እኔ ነኝ ያሸነፍኩ ብሎ ከበሮ ቢመታ፣ ለደጋፊ ይሁን ለተቃራኒ ለማሳመንም ይሁን ለመቀበልም ያስቸግራል ። መደረግ የነበረበት ቁም ነገር፣ ኣድማጭን ( ደጋፊ፣ ገለልተኛ፣ተቃዋሚ) ለማሳመን በሚያስችል መልኩ ማስረጃ መቅረብ ነበረበት። ማስረጃውም ዴሞክራስያዊ ሂደት ተከትሉ በፍትህ ተቅዋማት ለተኣማንነቱ ሰላማዊ ሙግት ማድረግ ይጠበቅበት ነበር። ከዚያ በኋላ የፍትህ ተቅዋማቱ የሚሰጡት ውሳኔ ምንም ይሁን ምን ከሚቀርቡ ግልፅ ማስረጃዎችና ሙጉቶች ኣድማጭ የራሱን ኣስተያዬት ብሎም ውሳኔ መስጠት ይችላል። በዚህ መልኩ የሚያድግ ዴሞክራሲ ለሸፍጠኛ የሆነ ሁሉ ማፈናፈኛ ያሳጣል ብዬ ኣስባሎህ። በመሆኑም የፀረ ዴሞክራሲ ኣስተሳሰብ ቦታ እያጣና ዴሞክራስያዊ ስርዓት እየጎለበተ የመሄድ ጉዳይ እውን ይሆናል።

በቅንጅት ስብስብ በኩል የነበረው ሁኔታ ግን ኣንድ ነገር ማለት እፈልጋሎህ። ራሱ እኔ ነኝ ያሸነፍኩ ብሎ የሚያውጅ፣ ከህግ ማእቀፍ መውጣት፣ የመሳሰሉት ነገሮች “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ ኣይብቀል ኣለች ኣህያ” የሚለውን ምሳሌ ኣስታወሰኝ። በህግ ኣግባብ ባለመሄዱ ብቻ ማንነቱ ያሳዬበት ወቅት እንደነበር መገንዘብ ይቻላል።

ገዢ ይሁን ተቃዋሚ ፓርቲ በቅድመ ምርጫ በወጡት የቅሬታ ማስተናገጃ መሰረት ከተጓዙ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ኣለው ብዬ ኣምናሎህ። ስለዚህ ከምርጫ 97 ዓ/ም የምንማርባቸው ቁም ነገሮች ብዙ ናቸው ለማለት እደፍራሎህ። እነሱም ከሁሉ በፊት

- ፍረጃ ይቁም
- በቅድመ/ድህረ ምርጫ የሚደረገው እንቅስቃሴ በወጣው የህግ ማእቀፍ መጓዝ
- መሸነፍና ማሸነፍ እንዳለ በስነ -ልቦና ዝግጅት ማድረግ

- የጥላቻ ፖለቲካ ማስወገድ
- ኣንድ ሰው ጥሩ/መጥፎ ነገር ቢሰራ በሰራው ልክ ከግለሰቡ ጋር ማያያዝ። ከብሄሩ ማያያዝ የለብንም
- መሬት ላይ ያለው የህዝብ ስሜት ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል (ራሳችን ባናነብ፣ ጎሳ እንጂ ብሄር የለም የሚል ሃሳብ ማስወገድ ብንችል)
- የዴሞክራሲ ባህልና ጉዞ በኢትዮጵያ ገና ጀማሪ መሆኑን ግንዛቤ መውሰድ
- እኔ ከሞትኩ ሰርዶ ኣይብቀል በሚለው ኣስተሳሰብ ኣለመመራት

## 5. ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ታሪክ ወሳኝ የሚባሉ የመንግስታት ለውጦች ኣጠር ባለ መልኩ ስንመለከት ቆይተናል። እነሱም

- ከኣክሱም ስርወ መንግስት ወደ ዛግዌ ስርወ መንግስት
- ከዛግዌ ስርወ መንግስት ወደ መለኮታዊ ዘውገ መንግስት
- ከመለኮታዊ ዘውገ መንግስት ወደ ደርጋውያን ስርዓት
- ከደርጋውያን ወደ ኢህኣዴጋውያን ስርዓት ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን

በዛግዌ ስርወ መንግስት የኣክሱምን ስልጣኔ ለማስቀጠል ሙከራ የተደረገበት ወቅት ስለ ነበር ከኣክሱም ስርወ መንግስት ጋር ኣንድ ላይ ማየቱ መልካም ነው እላለሁ። እናም በዛግዌ እና ቅድመ ዛግዌ በነበሩ መንግስታት የስልጣኔ ነፀብራቆች የሆኑ ቁሳዊ ኣሻራዎች ኣይተናል። ከዚህ የምንማርበት ቁም ነገር ያለ ይመስለኛል። ማለትም ለመስራት የሚያስችለን ሁኔታዎች ከተመቻቹ መስራትና ማደግ የምንችል ብሄር፣ ብሄረ ሰቦችና ህዝብች መሆናችን ማሳያውዎች ናቸው ብዬ ኣስባለሁ።

ከዛግዌ ስርወ መንግስት ወደ መኮታዊ ዘውገ መንግስት መሸጋገሩ ተከትሎ የተከሰቱ እውነታዎች፣

- በደቂቀ እስጢፋኖስ የስልጣኔና የዴሞክራሲ ጮራ ሲፈነጥቅ ተከታትሎ የማጥፋት ስራ ተሰርተዋል፣
- የገዳ ዴሞክራሳያዊ ስርዓት ማደግ ሲገባው እንዲደበዝዝ ተደርገዋል
- በኣኩሱምና በዛግዌ ስርወ መንግስታት የተጀመሩ የስልጣኔ ስራዎች ማስቀጠል ይቅርና ወደ ኋላ እንዲያንሸራትቱ /እንዲከስሙ ተደርገዋል ፣
- ከዛግዌ ስርወ መንግስት ወደ መለኮታዊ ዘውገ መንግስት ከተሻገረ በኋላ ለ700 ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች የህሊና እስረኞች እንዲሆኑ ተደርገዋል ፣
- በኣጠቃላይ የእደ ጥበብ ስራዎች እንዲዳከሙ ተደርገዋል

ከመለኮታዊ ዘውገ ስልጣን ወደ ደርግ ስርዓት ከተሻገረ በኋላም ቢሆን ፣ ከመሬት ላራሹ ከማወጅ በስተቀር በወሳኝ መልኩ ከኣፄዎች ተመሳሳይነት ነበረው ማለት እንችላለን ። በመሆኑም ከ 1270 ኣካባቢ ኣስከ 1983 ዓ/ም የጨለማ ዘመን ነበር ብንል እውነት ብዬ እወስዳለሁ። በመሆኑም ከኢኮኖሚ፣ ከሰብኣዊ መብት ኣያያዝ፣ ከዴምክራሲ ኣንፃር ሲታይ የድንቁርና፣ የፍዳ ግዜ ነበር ብንል ማጋነን ኣይሆንም ብዬ እወስዳለሁ።

**ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ ግን ብሄር ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች**

- ራስን የማስተዳደርና ኣካባቢን የማልማት ስልጣንና ነፃነት ህብረተ ሰቡ ኣጣጥሞታል
- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ኣባላትና የክልል ባለስልጣናት የወከላቸውን ማህበረሰብ ጥቅም ለማስከበር የመደራደር ኣቅማቸው ኣጎልብተዋል።

ስለዚህ ከእንግዲህ ኢትዮጵያ የምትባል ኣገር ልትኖር የምትችለው ሁሉም የኛ/የራሳችን ብሎ ሲቀበል እንጂ የኣንድ የተወሰነ ቡድን ውሳኔ የመቀበልን ኣግባብ ያበቃ ይመስለኛል ። በመሆኑም **ተከባብሮና ተቻችሎ በ "የጋራ ተጠቃሚነት" መርህ ነው መጓዝ ያለብን የሚመስለኝ።** በዚህ መልኩ ከተጓዝን ውጤቱ እየታዬ ነው። በ25 ዓመታት ውስጥ ተስፋ ሰጪ የሆኑ ምልክቶች ታይተዋል። በመሆኑም ታላቁ የህዳሴ ግድብ ጨምሮ ብዙ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እየተገነባ ይገኛለን። በኣለም ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስምዝገብ ላይ ካሉት ኣገራት ተርታ ኢትዮጵያ ኣገራችን ተሰልፋለች። ስለ ኢትዮጵያ እድገትም የኣጭርና የረዥም እቅዶች ተነድፈው መንግስትና ህዝብ በእንቅስቃሴ ላይ ናቸው። በዚሁም መሰረት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ኣገሮች ተርታ ለመሰለፍ በእቅድ ተቀምጠዋል። በወሬ ብቻ ሳይሆን የኣገራችን እድገት ማሳያዎች ሊሆኑ የሚችሉ በተግባር እየታዩ ነው። ለምሳሌ በ2008ዓ/ም ከ10 ሚልዮን በላይ በድርቅ የተጎዳው ህዝብ ለመቋቋም ተችለዋል፣ እንዲሁም የነበረው ኣመፅ በመሸከም ኢትዮጵያ እያደገች መሆኗን በኣለም እየተመሰከረ ነው ።

በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ በማወቅ ይሁን ባለማወቅ ኣንዳንድ የውጭ ሚድያዎች (ዘሃበሻ ፣ የኣመሪካ የኣማርኛ ድምፅ ራዲዮ ፣ኢሳት ወዘተ) ኢትዮጵያ ያለችበት ደረጃ ሳይረዱ ይመስለኛል የብሄር ፌደራሊዝም /ብሄርተኝነት ሲያወግዙ፣ ብሄርተኝነት ሲያጥላሉ፣ የጥላቻ ፖለቲካ ሲያሰራጩ ይደመጣሉ። በእንደዚህ ዓይነት መሰሪ ፕሮፓጋንዳና፣ የመንግስት የማስፈፀም ውስንነትን ተደምሮ ቀላል ህዝብ የማይባል ማንቀሳቀስ ችለለዋል ማለት ይቻላል ። የ2008ዓ/ም ኣመፅ በማሳያነት መውሰድ ይቻላል። ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የምናስብ ከሆነ፣ የሚተላለፈው ፕሮፓጋንዳ በየተኛውም መልኩ ለኣሁኑዋ ኢትዮጵያ የሚመጥን ኣይደለም። ምክንያቱም በየክልላችን ያለው የመንግስት ቁመና የሚያመለክተው ማንም ከማንም ኣጃጅሎ ሃብት የሚዘርፍበት ሰኣት ኣይደለንም ያለነው። ስለዚህ በ **የጋራ ተጥቃሚነት መርህ** ተከትለን ከሄድን ዴሞክራሲያችንም ሆነ ኢኮኖሚያችን ያድጋል ብዬ ኣስባሎህ። **ነገር ግን ብሄር ተኮር ፌዴራሊዝም/ብሄርተኝነት/ ጎልቶ በወጣበትና ከገርዎች የተለጠጠ የኋላ ቁርሾ ባለበት ኣገር ብሄርተኝነት ማጥላላት፣ ጥላቻ እንዲነግስ ማድረግ፣ ኣንዱን ብሄር ከፍ ኣድርጎ ሌላውን ጎሳ ነው ማለት ፣ ህገ ኣራዊት ወዘተ ብሎ መስበክ በተቀጣጠለ እሳት ላይ ቤንዚን የማርከፍከፍን ያህል ሊቆጠር ይችላል።** የብሄርና ብሄረ ሰብ ሙብቶችን በማረጋገጡ ያልተዋጠላቸው ኣስተሳሰብ ውስጥ ከዋኘን ግን እንደኣገር ለባሰ ኣደጋ ከመጋልለጥ በስተቀር የሚያመጣው ለውጥ ኣለ ብሎ ማሰብ ራስን ማሞኘት ነው።